# የመኢአድ ድጋፍ በዩናይትድ ኪንግደም

# መቋቋም መግለጫ

የቅንጅት አመራር በእስር በነበረበት ጊዜና ከእስር ከተለቀቀም  በኋላ በአመራሩ መካከል በነበረዉ ችግር ሳቢያ አብዛኛዉ የዲያስፖራ ደጋፊ ግራ ተጋብቶ እንደነበር ይታወሳል። እኛ በእንግሊዝ አገር የምንገኝ ደጋፊዎች በልዩ ልዩ መልክ እየተሰባሰብን ሂደቱን ስንከታተል ቆይተናል። ከዚያም ልዩነቶች እየጎሉ ሲመጡ “የኢትዮጵያ ህዝብ ድምጽ ድጋፍ ኮሚቴ በዩናይትድ ኪንግደም” በሚል መጠሪያ ስም ተደራጅቶ ላለፈው አንድ አመት ሲንቀሳቀስ የቆየዉ ስብስብ ታህሳስ 18 2001 በተጠራው ስብሰባ ተጨማሪ አዳዲስ አባላት በተገኙበት ሰፋ ያለ ዉዪዪት ካደረገ በኋላ የሚከተሉትን ዉሳኔዎች አሳልፏል፦

፩ ድምጹን የተቀማዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ከምርጫ 97 በኋላ የደረሰበትን ሰቆቃ በማገናዘብ በአሁኑ ጊዜ በህዝቡ መሀል ያለዉን የትግል ስሜትና እምቢተኛነት በሰፊዉ ተወያይቶ የጋራ ግንዛቤ ላይ ደርሰዋል።

፪ ይህንንም የህዝብንና የሃገር ማዳን ትግል ለመምራት ብቃት ያለው ብቸኛ ሃገራዊ ድርጅት የመላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ነዉ የሚል ዉሳኔ ላይ ደርሷል።

፫ በዚህም ላይ በመመስረት ድርጅታችን እስካሁን የተጠቀመበትን መተዳደሪያ ደንብ ካለዉ የኢትዮጵ ፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማመሳሰል አሻሽሎ ራሱን የመላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ድጋፍ በዩናይትድ ኪንግደም (የመኢአድ ድጋፍ/በዩኬ) በሚል ይፋ ወጥቷል።

፬ የዚህ የድጋፍ እንቅስቃሴ ዋና አላማ መኢአድን በቁሳቁስ፤ እና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን በአካተተ ተግባር መርዳት ይሆናል።

፭ ይህ የድጋፍ እንቅስቃሴ በዩናይትድ ኪንግደም የሚኖሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ትግልና የመኢአድን ራእይ የሚደግፉ ኢትዮጵያዉያኖችን በሙሉ የድርጅቱ ተሳታፊ አባል እንዲሆኑ ጥሪ ያቀርባል።

የመኢአድ ድጋፍ በዩናይትድ ኪንግደም
AEUP Support UK
Email: aeupdigafuk@yahoo.co.uk
ሎንደን ዩናይትድ ኪንግደም/ London UK